# አክብሮትና ድጋፍ ለኀሊና እስረኞ

የትም ይሁን መቼም፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በተወሳ ቁጥር ፣ ዘወትር የማይዘነጋዉ ቁምነገር የዘጐቿ የመስዋዕትነት ገድል ነዉ። ሀገራችን ነፃነቷንና ሉዐላዊነቷን ጠብቃ ለዚህ ትዉልድ ዘመን የበቃችዉ ቀዳሚዉ ትዉልድ በከፈለዉ የሕይወት ፣ የደምና የላብ ዋጋ መሆኑ አያጠያይቅም። ይህ ትግልና መስዋዕትነት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተሸጋገረና እየተወራረሰ እነሆ የዛሬዉም ትዉልድ ፅዋዉን ከቀዳሚዎቹ በክብር ተቀብሎ የራሱን ታሪካዊ ሚና በመጫወት ፣ ድርሻዉንም በመወጣት ላይ ይገኛል።

ይህ ፣ የታፈራችና የተከበረች ብቻ ሳይሆን የበለጸገች ኢትዮጵያን ለተተኪዉ ትዉልድ የማዘጋጀቱ ዘርፈ-ብዙ ትግል ዛሬም በርካታ ሀቀኛ ልጆቿን ዋጋ እያስከፈላቸዉ መገኘቱ እዉነት ነዉ። ሀገራችንን ከድህነት መዝገብ ለማስፋቅ እየተደረገ ካለዉ ጥረት ጎን ለጎን ፣ የዜጎቿ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ፣ የሕግ የበላይነት በሠፈረበት ሕዝባዊ ሥርዓት መተዳደር እንዲችሉ ለማድረግ የሚካሄደዉ ትግል እንደ ቀጠለ ይገኛል።

ትግሉ ዘርፈ-ብዙ የመሆኑን ያህል እየጠየቀ ያለዉም ዋጋ ከባድና ዉስብስብ ነዉ። በርካታ ወገኖቻችን ለሠላምና ለዴሞክራሲ ስፍነት ሲሉ ሕይወታቸዉን ሰዉተዋል፤ በርካቶች ዛሬም ድረስ ያለፍርድ ወይም በተዛባ ፍርድ አማይካይነት በየእስር ቤቱ ታጉረዋል። በሺህዎች የሚቆጠሩ የሀገራችን ዜጎች ከግፈያ ፣ ከስቃይና ከእንግልት ለማምለጥ ሀገራቸዉን ጥለዉ በየባዕድ ሀገር በስደት ተበታትነዋል።

ትናንት ከትናንት ወዲያ የኢትዮጵያን ነጻነትና አንድንት በማስከበሩ ተጋድሎ ዉስጥ ለታሪክ ተጠቃሽነት የበቁ አያሌ የቁርጥ ቀን ዜጎች እንደመኖራቸዉ ሁሉ፣ዛሬም ለፍትህና ለሕግ የበላይነት መረጋግጥ የግንባር ሥጋ ሆነዉ፣ በእምነታቸዉና በእዉነታቸዉ ፀንተዉ በመፋለም ለአርአያነት የበቁ ወጣት የሠላማዊ ትግል ጀግኖች አሉን። ከእነዚህም ዜጎቻችን መሐከል ለእምነቷ ፅኑእና

ቀናኢ በመሆን ራሷን ለመስዋዕትንት ያቀረበችዉን ወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳን የምናወሳዉ ቆራጥነቷን አብነት በመጥቀስ፣ የመንፈስ ፅናቷን በማወደስ ነዉ።

በተለያዩ አስዳጅ ምክንያቶች ሀገራችንን ጥለን በመሰደድ በአሁኑ ወቅት በሰሜን አሜሪካ ቴክሳስ ግዛት በሂዩስተን ከተማ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን፣ ለብርቱካን ሚዴቅሳና ለሌሎችም በሺህዎች ሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን የኅሊና እስረኞች ያለን አድናቆትና ክብር ቃሎች ከሚገልፁት በላይ ይገዝፋል።

ይህንኑ የአክብሮትና የድጋፍ ድምፃችንን በጋራ ለማሰማትና የትግል አጋርነታችንን ለመግለፅም ፣ እ.አኤ. አቆጣጠር ፌብሯሪ 6 ቀን 2010 አንድ ሕዝባዊ መድረክ በሂዩስተን ከተማ አዘጋጅተናል።

ይህ መድረክ ፣ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት፣ ለፍትሕና ለሕግ የበላይነት ተቆርቋሪ በሆኑ ዜጎች አማካይነት የተዘጋጀ ሲሆን ፣ በሥነ ሥርዓቱም ላይ የብርቱካን ሚዴቅሳ ብርቱ የትግል መንፈስ እየተዘከረ ሌሎችም የኅሊና እስረኛ ወገኖቻችን የሚታወሱበት፣ የሚታሰቡበት... ይሆናል።

በዚህ የአክብሮትና የድጋፍ መግለጫ ሥነ ሥርዓት ላይ የአምኒስቲ ኢንተርናሽናል ተወካይ ፣ የአፍ የፍትህ ምክር ቤት መሥራችና መሪ አቶ ኦባንግ ሚቶ በክብር እንግድነት ተጋብዘዋል። የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኅበር አንጋፋ አባላት በመድረክ መሪነት በሚሳተፉበት በዚህ ዝግጅት ላይ አንጋፋዉ አርቲስት ሻምበል በላይነህ በጣዕመ ዜማዎቹ የዝግጅቱን ተሳታፊዎች ያዝናናል። የኅሊና እስረኞቹንም ያወድሳቸዋል።

የዚህ መድረክ አዘጋጆችና ተሳታፊዎች እንደሚያምኑት ፣ ዛሬ ሀገራችን ያለችበት ሁለንተናዊ ችግር በተወሰኑ ወገኖች መልካም ፈቃደኝነትና ጥረት ብቻ አይቃለልም። የሁሉንም ኢትዮጵያዊ በፍቅርና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ቅንጅ ተሳትፎ ይጠይቃል።

የሀገራችንን ዜጎች የመብት ጥያቄም በእስራት ፣ በአፈናና በግድያ መመለስ ወይም ማስቆም እንደማይቻል ሊታመን ይገባል።በተለይም የሀገራችንን ፖለቲካዊ ችግሮች ለመቅረፍ ሁነኛዉ መፍትሔ ወደ ብሔራዊ መግባባት የሚያዳርሰዉን ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ አግባብ መከተል የሁሉም ወገኖች ቀዳሚ ምርጫ መሆን ይኖርበታል።

ይህንኑ የሰለጠነ አማራጭ እውን ለማድረግም ዛሬ በኢትዮጵያ ሀገራችን በሥልጣን ላይ የሚገኘዉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ፣ የዜጎችን የመደራጀት፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት እንዲያከብር፤

ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸዉን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ፤

ነፃዉ ፕሬስና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሥራቸዉን በነፃነትና በኃላፊነት ስሜት እንዲያከናዉኑ ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ እንድደረግላቸዉ፤

በመጨረሻም ፣ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳና የፖለቲካ አቋማቸዉ ልዩነት ፣ እንዲሁም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸዉን ለመገልገል በመሞከራቸዉ ፍትህ ተነፍገዉ እስር ቤት ዉስጥ ሕይወታቸዉን በመግፋት ላይ የሚገኙ የኅሊና እስረኞች የሆኑ ወገኖቻችን፣ ሀገራቸዉን በማሳደግ ሁለንተናዊ ጥረት ዉስጥ አስተዋጽዖአቸዉን ያበርክቱ ዘንድ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲለቀቁ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲ ፣ ለፍትህና ለሕግ የበላይነት የቆሙ ወገኖች ሁሉ በሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ላይ አስፈላጊ የሆነዉን ግፊትና ጫና እንዲያበረቱ፤

ለኅሊና እስረኞቹም አክብሮት እንዲቸሩዋቸዉ፣ለቤተሰቦቻቸዉም አስፈላጊዉን ድጋፍ እንዲያደርጉላቸዉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**እግዚአብሔር ሀገራችንና አንድነታችንን ይባርክ!**

**ለሠላም፣ለዴሞክራሲ፣ለፍትህና ለሕግ የበላይነት ተቆርቋሪ የሂዩስተን ከተማ ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን**

**ፌብሯሪ** 2010